**የውጭ ታዳሚዎች ተደጋጋሚ ጥያቄዎች - ኢትዮጵያ**

**ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን የCOVID-19 መልሶ መቋቋም እና መመከት ፕሮግራም**

**ሚያዚያ 2012 ዓ.ም**

---

## COVID-19 የሚያሳድረው ተጽዕኖ

ኮቪድ19 እየተስፋፋ ሲመጣ፣ አስከፊ ጉዳቱ ይበልጥ እየታየ ይሔዳል። የሕዝብ ጤና ቀውስ በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ተባብሷል - የሥራ ማጣት ፣ የትምህርት ቤት መዘጋት ፣ ድህነት፤ እነዚህ ተፅእኖዎች በአፍሪካ እና በካናዳ ውስጥ በሚገኙ የአገሬው ተወላጅ ማህበረሰቦችን ጨምሮ በአለም አቀፍ ደረጃ ተጋላጭ የሆኑ ህዝቦች የተሸከሟቸው ናቸው ። በጊዜ መፍትሔ ካላበጀን ወረርሺኙ በከፍተኛ ልፋት የተገኙ የልማት ውጤቶችን በማጥፋት ማህበራዊ መረጋጋትን አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል ።

## ተቋማት እና ማህበረሰቦች ተጠቃሚ ማድረግ

የታመንን አጋር እንደመሆናችን ፣ ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ዓለም አቀፍ ፈተናን ለማሸነፍ ከመንግስታት ፣ የግሉ ሴክተር ፣ የትምህርት ተቋማት ፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች እና ወጣቶችን ጨምሮ ከአጋሮቹ ጋር ይቆማል። በዚህ ቀውስ ውስጥ አጣዳፊ ፍላጎቶችን ለማስተናገድም ለአዳዲስ አጋርነቶች ክፍት ነን ።

የማስተርካድ ፋውንዴሽን ኮቪድ-19 የመልሶ መቋቋም እና መመከት ፕሮግራም አፍሪካ ውስጥ ያሉ ተቋማትና ማህበረሰቦች እንዲሁም በካናዳ ውስጥ የሚገኙ የአገሬው ተወላጅ ማህበረሰቦች የዚህን ወረርሽኝ

የአጭር ጊዜ ተፅኖዎች ለመቋቋም እና ምላሽ እንዲሰጡ ያግዛቸዋል ፣ በረጅም ጊዜ የመቋቋም አቅማቸውንም ያጠናክራሉ ። እንዲህ በማድረግም አንድነታቸውን ጠብቀው፡ ኢኮኖሚያቸውን መልሶ እንዲያገግም እንዲሰሩ ያደርጋል።

የማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ኮቪድ-19 መልሶ መቋቋም እና መመከት ፕሮግራም ለወጣቶች እና ለማህበረሰቦች ድጋፋችንን ከመመለስ ይልቅ የበለጠ አጠናክረን እንድንሰጥ ያስችለናል።

በጋራ ፣ ከአጋሮቻችንና ከሌሎች ጋር በመሆን ወጣቶችን በተለይም ወጣት ሴቶችን ጥራት ያለው ትምህርት፣ ክህሎት ፣ የገንዘብ አገልግሎት እና የተሻለ ሥራን እንዲያገኙ ለማድረግ እንሰራለን ።

## <u>የፕሬዚዳንታችን እና ዋና ስራ አስፈጻሚያችን ሬታ ሮይ መልዕክት</u>

ይህ ፕሮግራም ሁለት መሠረታዊ ዓላማዎች አሉት። በመጀመሪያ፣ የሚከተሉትን  አስቸኳይ ፍላጎቶችን ለማስተናገድ ፦

- ለጤና ሰራተኞች እና የመጀመሪያ ምላሽ ሰጭዎች ድጋፍ።
- ለተማሪዎች የድንገተኛ ጊዜ ገንዘብ መስጠት ።

ይህንን እንደ ተቀዳሚ ጉዳይ እንፈፅማለን።

ሁለተኛው ደግሞ የአሁኑን እና የወደፊቱን ችግሮች የመፍታት አቅም ላላቸው እና ኢኮኖሚው በፍጥነት እንዲያገግም  ለሚያግዙ ፕሮጀክቶች ድጋፋችንን በእጥፍ ማሳደግ ይሆናል። በተለይም በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ በትኩረት የምንሰራ ይሆናል ፦

- **ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅርቦትን መጨመር-** እነዚህ ተቋማት አሰራራቸውን ወደ ዲጂታላይዜሽን እንዲያሳድጉ፣ የኮቪድ 19 የኢኮኖሚ ተጽዕኖን ተቋቁመው እንዲቆዩ እና ምናልባትም የጤና ስርዓቱን የሚያግዙ ምርቶችን እንዲያመርቱ እና እንዲያቀርቡ ማገዝ።

• **የኢንተርኔት ትምህርት እንዲኖር ማስቻል** - በወረርሽኙ ምክንያት ትምህርታቸው የተቋረጠባቸው ወጣቶችን ለማገዝ ሲሆን ይህም ከትምህርት ተቋማት ጋር የሚሰራ ይሆናል። በሂደቱም ተቋማቱ ተማሪዎቻቸው ለመቆጣጠር፣ ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ እና ፈተና እንዲወስዱ የሚያስችላቸው ሲሆን ይህ አይነቱ እርምጃ የትምህርት ተቋማትን ለመሰል ቀውሶች እንዲዘጋጁ ብቻ ሳይሆን የትምህርት ሁኔታን እስከወዲያኛው የሚቀይር ነው።

• **ዲጂታል መፍትሄዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማገዝ** - መሰረታዊ ለሆኑ እንደ የፋይናንስ ስርዓት፣ የምግብ ምርት እና አቅርቦት፣ ቤቶች እና ግንባታዎች፣ ትራንስፖርት እና ማጓጓዝ ፣ የህብረተሰብ ጤና መጠበቂያዎች ምርት እና አቅርቦት ላሉ አገልግሎቶች ማደግ የዲጂታል ስርዓቱ ጥሩ በሆኑባቸው አካባቢዎች ከሌላቸው አንጻር የተሻሉ እንደሆኑ ይታወቃል።

እነዚህን ተግባራት በመፈጸም እና የተለያዩ ተቋማትን አቅም በማጠናከር ይህንን ዓለምአቀፍ ወረርሽኝ መመከት እንችላለን። በሌላ በኩል ደግሞ ይሄ ወረርሽኝ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመከላከል እና ወደ ጤናማነት ለመመለስ ህብረተሰቡ ተነሳሽ ሆኖ ፣ ተቋማትም ዝግጁ ሆነው ለማየት እንፈልጋለን።

## ኢትዮጵያ

### 1. በ“ማስተርካርድ ፋውንዴሽን የኮቪድ-19 መልሶ መቋቋም እና መመከት ፕሮግራም” በኢትዮጵያ ትኩረት ያደረገው ምን ላይ ነው?

**በኢትዮጵያ አምስት ቁልፍ ዓላማዎች አሉ፡**

**1**. <MMEs> ከነአቅማቸው እንዳሉ ማረጋገጥ ፣ አዳዲስ እና ጊዜውን የሚመጥኑ ስራዎችን በመፍጠር ሰራተኞቻቸውን ማቆየት እና ከማስተርካርድ ፋውንዴሽን የኮቪድ-19 የመልሶ መቋቋም እና መመከት ፕሮግራም የድርጅት ብድር ዋስትና ጋር አብረው እንዲሰሩ ማድረግ።

**2**. የቫይረሱ ስርጭትን እና ሊከሰት የሚችለውን ተፅእኖ ለማስቀረት የዲጂታል ፈጠራን መደገፍ።

**3**. ለትምህርት ተቋማት ኦንላይን - ተኮር ትምህርትን እንዲተገብሩ ሥልጠናን ማበረታታት።

**4**. የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ተነሳሽነት ላይ ተሳትፎን ማሳደግ።

**5**. አቅም ያላቸው አምራች ኩባንያዎች ወደ ህክምና አቅርቦቶች ማምረት እንዲችሉ እና አፋጣኝ ፍላጎቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ መስጠት።

1) **‹MMEs› ከነአቅማቸው እንዳሉ እና ሰራተኞቻቸውን ማቆየታቸውን ማረጋገጥ** - የድርጅት ማዳን እና መልሶ ማቋቋሚያ የብድር ዋስትና አቅርቦት፡ የተቋማትን መዘጋት እና የሥራ ማጣትን ለመቀነስ ሲባል የተፈጠረ ስርዓት ነው። አቅርቦቱ ተቋማቱ ከቀውሱ እንዲያመልጡ፣ ሠራተኞቻቸውን እንዳያሰናብቱ እና ከድህረ - ኮቪድ 19 በኋላ እንደገና በአነስተኛ አቅምም ቢሆን ወደ ስራ እንዲመለሱ ለማነቃቃት የተመደበ ነው። ሶስት የድርጅት ምድቦች ባላቸው የተጋላጭነት መጠን እና ከሌሎች አጋዦች ጋር በመሆን ባላቸው የመቋቋም ችሎታ ተልይተው ዒላማ ይደረጋሉ።

**ሀ. ከፍተኛ ተጋላጭነት-** የተመዘገቡ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ኢ-መደበኛ ድርጅቶች (ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ)

**ለ**. **መለስተኛ ተጋላጭነት** - ከአገልግሎት-ጋር የተዛመዱ ጥቃቅን አና መለስተኛ የንግድ ሥራዎችን የሚሰሩና በከፍተኛ ሁኔታ የትዕዛዝ ማሽቆልቆል ወይም የትእዛዝ ስረዛ ሊያጋጥማቸው የሚችሉ።

**ሐ**. **ዝቅተኛ ተጋላጭነት** - በአብዛኛው መካከኛ ኢንተርፕራይዞች ያላቸው እና በአገልግሎት እና በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ውስጥ ገቢያቸው ቀስ በቀስ ማሽቆልቆል የሚያገኛቸው እና ነገር ግን ይህ ነው የሚባል የንግድ ስራ መቋረጥ ወይም የትዕዛዝ ስረዛዎች የማያጋጥሟቸው።

2) **የዲጂታል ፈጠራን መደገፍ** - የቫይረሱ ስርጭትን እና ሊከሰት የሚችለውን ተፅዕኖ የሚያስቀሩ ፈጠራዎች ወሳኝ ናቸው። በዚህ ቀውስ ውስጥ የሚተገበሩት የዲጂታል ፈጠራ እና ስርዓቶች ከዘመኑ ወረርሽኝ ባለፈ የሚቆዩ እና ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸው ናቸው።

- **የርቀት ሥራ / ትምህርት፡-** የርቀት ሥራ እና የርቀት ትምህርት የሚያመቻቹ ዲጂታል መፍትሔዎች በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ተፈላጊነት አላቸው ።

- **ካለጥሬ ገንዘብ የሚከፈል ክፍያ እና የገበያ ቦታ፡-** የገንዘብ ኖቶች የኮሮና ቫይረስን እንደሚያስተላልፉ በመታወቁ እና የአገልግሎት አሰጣጣቸውም ይህን ያህል አመርቂ ባለመሆኑ ለዲጂታል ክፍያ / ሞባይል ክፍያዎች እና ለዲጂታል የገበያ ቦታዎች አዲስ ዕድል ይዞ መጥቷል፡፡

- **ዲጂታል ፈጠራ ለኮቪድ-19 መፍትሔዎች፡-** ተፈላጊው ኢንቨስትመንት ቀድሞውኑም በቦታው የሚገኝ በመሆኑ፡ የኮሮናቫይረስ ስርጭትን የሚቀንሱ ፈጠራዎችን ለመደገፍ ፣ ለመመርመር ፣ ለመከታተል እና ሌሎች በርካታ የህክምና አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ማድረግ ወቅታዊ ጉዳይ ሊሆን ይገባል፡፡ እንደነዚህ ያሉት ፈጠራዎች ሕይወት ለማዳን እና የሕክምና እንክብካቤን ለማድረግ ይጠቅማሉ፡፡ በተጨማሪም ፕሮግራሙ የኮቪድ-19 መፍትሄዎችን ለማዘጋጀት የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን ውድድር ውስጥ ያስገባል፡፡

- **የኢ-ኮሜርስ መድረክን ማበልጸግ እና ማስተዋወቅ እንዲሁም በቴክኖሎጂ የታገዘ ድጋፍ አሰጣጥ እና አቅርቦትን ማስተዋወቅ፡-** የኢ-ኮሜርስ እና የአቅርቦት ኩባንያዎች ቁልፍ የሎጂስቲክስ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ከቤት ያለመውጣት እርምጃዎች የሸቀጣ ሸቀጦችን በቤት ውስጥ የመፈለግ ፍላጎትን ከፍ ሲያደርጉ የኢ-ኮሜርስ ኩባንያዎች ያለንክኪ አቅርቦትን የሚያሟሉ መተግበሪያዎችን ፈጥረዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ለተጠቃሚዎች ፣ ለአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እና ለአምራቾች እጅግ ጠቃሚ ሆኗል፡፡

3) **ለትምህርት ተቋማት ኦንላይን - ተኮር ትምህርትን እንዲተገብሩ ሥልጠናን ማበረታታት -** የመማሪያ ተቋማት መዘጋት በርቀት እና በኦንላይን ትምህርት ላይ ከፍተኛ ፍላጎት ፈጥረዋል። በዚህ የችግር ጊዜ ውስጥ የመማር እና ማስተማር ቀጣይነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ፡፡ መርሃግብሩ በዚህ ወረርሽኝ ወቅት የርቀት ስልጠናን መስጠት እንዲቻል የኦንላይን ትምህርትን ማጠናከር ላይ እገዛ ያደርጋል፡፡

***4)* በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ተነሳሽነት ውስጥ ተሳትፎን ማሳደግ** - በመላ አገሪቱ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዛፎችን ለመትከል እቅድ በማውጣት እና በመተግበር አሁን ላይ ከስራ ውጭ የሚገኘውን የግንባታ እና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የጉልበት ሰራተኛ በመጠቀም እግረ መንገድም ለሰራተኛው የስራ እድል በመፍጠር ዓለም አቀፍ እና አካባቢያዊ የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን መፍታት ይቻላል ፡፡

**5) አቅም ያላቸው ኩባንያዎችን ወደ ህክምና አቅርቦቶች ማምረት መመለስ** - በስራ ላይ የሚገኙ ኩባንያዎችን (ለምሳሌ በጨርቃ ጨርቅ ውስጥ ያሉትን) ምርታቸውን ወደ ኮቪድ-19 የህክምና መሳሪያዎች እና ወሳኝ አቅርቦቶች (ጭንብሎች ፣ ንፅህና መጠበቂያዎች ወዘተ) እንዲዛወሩ ማበረታታት፡፡ ይህ ቫይረሱን ለመዋጋት፣ እየጨመረ የመጣውን የአካባቢ ፍላጎት ለማርካት ይረዳል፣ እንዲሁም ምርቶችን ለመላ አህጉሩ ለማቅረብም እድል ይሰጣል፡፡

**አስቸኳይ ፍላጎቶችን መደገፍ** - ለጤና ሰራተኞች የድጋፍ አቅርቦትን፣ የመጀመሪያ ምላሽ ሰጭዎችን፣ እና የፊትለፊት የሚጋፈጡ ተቋማትን፣ የህብረተሰብ የጤና ዘመቻዎችን፣ የተማሪዎችን የአስቸኳይ ጊዜ ገንዘብ እና የመከታተያ መሳሪያዎችን ማቅረብን እና የመሳሰሉትን ያካትታል ፡፡